# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት**

ቀን፡ **7/4 - 7/6/2019**
**አድራሻ፡** W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941 (Takes about 3 hours to 3:30 hours)
**Phone** = (920) 294-3323 Booking ID number= 14589
For making reservation please call during the below hours
**Sunday - Thursday 8:30-4:30**
**Friday - Saturday 24 hours**
**When reserving rooms please provide the date, the name Yemsrach how many people will be in the room.**

**የአምልኮና የቃል ጊዜ ከወንድም ጌታያውቃልና ከእህት ብሩክታይት ጋር**

በApril 14 ለያት ያለ የአምልኮና የቃል ጊዜ ከወንድም ጌታያውቃልና ከእህት ብሩክታይት ጋር ይኖረናል። ስለዚህ ፕሮግራም እየጸለያችሁ እንድትቆዩ ደግሞም በዚህ ፕሮግራም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድትሆኑ እናበረታታችኋለን። ጌታ ይባርካችሁ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።
(ያዕ. 5:16)

| | |
|---|---|
| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m. |
| **March 31, 2019** | **መጋቢት 22፣ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | እህት ሒሩት ተስፉ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| ቃል ............. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።"

(2ዜና 7:14)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ።

*"በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።" (2 ዜና 7:14)*

ክርስቲያኖች ካሉን ተስፋዎች መካከል በከፍተኛ ስፍራ የምናስቀምጠው አንዱ አምላካችን እግዚአብሔር ጸሎትን ሰምቶ የሚመልስ መሆኑ ነው። በዚህ ስፍራ እንደምናነበው እግዚአብሔር በስሙ ለተጠሩት ሕዝቡ የገባው ተስፋ አለ። ተስፋው ግን ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። የመጀመሪያው በእግዚአብሔር ፊት ትሁት መሆን ነው። ሁለተኛው የእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መፈለግ ነው። ሶስተኛው ከክፉ መንገድ መመለስ ነው። ይህ ሲሆን እግዚአብሔር ይሰማናል፣ ይቅር ይለናል፣ ደግሞም ይፈውሰናል።

ለሚገጥሙን ማንኛውም ግላዊና አገራዊ ጉዳዮች ትልቁ መፍትሔ በእግዚአብሔር ፊት በትህትና መጸለይ ነው። በአውዱ ላይ እደምንመለከተው ይህ ትልቅ የጸሎት መልስ ተስፋ የተሰጠው አገራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን ለመቅጣት ዝናብን ቢከለክል፣ ምድሪቱን ይበላ ዘንድ አንበጣን ቢያዝ ወይንም ቸነፈርን ቢያዝዝ ለዚህ አገራዊ ችግር መፍትሔ ያለው በስሙ በተጠሩት ህዝቡ ዘንድ ነው። አሳሳቢ ሁኔታዎች ሲገጥሙ በትህትና በታላቁ ጌታ ፊት በጸሎት መውደቅ ወሳኝ ነው። በተለይም ቤተ ክርስቲያን ዋናው ማድረግ ያለባት ይህ መሆን አለበት። የራሳችንን ማስተዋል ተጠቅመን ችግሩን ለመፍታት ከመጣር ይልቅ አስቀድመን እግዚአብሔር ሆይ አባክህን ይህንን ጉዳይ ተመልከተው ብለን በጸሎት ብንቀርብ መልስ ከሰማይ ይመጣልናል።

የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ወደ እርሱ በምልጃ መሮጥ ነው። እርሱን የሙጥኝ ማለት ነው። ሰው በመከራው ጊዜ የበለጠ የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ አለበት። የአገር ሸክም የከበዳቸው አባቶች ያደርጉ የነበረው የሕዝባቸውን መተላለፍ ይዘው ፊቱን መፈለግ ነው። ነህምያ የኢየሩሳሌምን መፍረስና መቃጠል ሲሰማ ለአያሌ ቀናት በጾምና በጸሎት በንስሃም የእግዚአብሔርን ፊት ፈለገ። በእግዚብሔር ፊት እንደ መሪ የሕቡን መተላለፍ ይዞ ቀረበ። አለቀሰ። ነስሃ ገባ። ነህምያ መፍትሔ ፍለጋ ያገለገለው ወደ ነበረው ንጉስ አልገባም። ወይንም አስቀድሞ ችግሩን ለመፍታት አልተንቀሳቀሰም። ነገር ግን አስቀድም የአምላኩን ፊት በጽኑ ፈለገ። ቃል-ኪዳኑን አስታወሰ። ምሕረትና ሞገስን ጠየቀ። እግዚአብሔርም ዘምበል አለለት። ዳንኤልም የኢየሩሳሌም የሰባ አመት ምርኮ የሚፈጸምበትን ከመጽሐፍ ሲረዳ ያደረገው አንድ ነገር በንስሃ የአምላኩን ፊት መፈለግ ነበር።

ወገኖቼ:- ለችግራችን መፍትሔ ያለው በእግዚአብሔር እጅ ነው። አይኖቻችንን ወደ ተራሮች ብናነሳ እርዳታ አናገኝም። እርዳታችን ያለው ከሰማይ አምላክ ዘንድ ነው። ለምንኖርባት ከተማ ችግርም ሆነ ለተወለድንባት አገር ችግር እግዚአብሔር ምህርትን የሚያደርገው በሰሙ የተጠራነው ህዝቡ እራሳችንን አዋርደን እንደ ነህምያ በጸሎትና በንስሃ በፊቱ ስንቀርብ ነው። ያን ጊዜ የሰማይ አምላክ ይሰማናል። ይቅር የለናል። ስብራታችንንም ይጠግናል። አሜን!